# ሰይፉ እና እባቡ

## በ ኤል. ቬረ ኤሊኦት

*(የሚከተለው ራእይ በ1970ቹ መጨረሻ ለኤል. ቬረ ኤሊኦት (L. Vere Elliott) ተሰጠ)*



የመጽሐፉ ርዕስ በእንግሊዝኛ “The Sword and the Serpent” የሚል ነው።

ራእዩ ይህ ነው። እኔ በአንድ ታላቅ የስብሰባ አዳራሽ (ቤተ ክርስቲያን) መሐል ነበርሁ፥ ግድግዳዎቹና ጣሪያዎቹም በከበሩ ድንጋይ ፈርጦችና ጌጣ ጌጦች ተሸፍነው ነበረ፥ መስኮቶቹም ከባለቀለም መስታወት ነበረ የተሰሩት (እንደ ካቴድራል ወይም ቤተ ክርስትያን ዓይነት)። አዳራሹ በሰዎች ተሞልቶ ነበር፥ አንዳንዶች ሀብታም፣ አንዳንዶች ድሀ፣ አንዳንዶች ህሙማንና አንካሶች፣ የማይናገሩና እውራን ነበሩ፤ ነገር ግን ሁሉም ሰንሰለቶች ነበረባቸው እና በካቴና ታስረው ነበር፥ አንድም ነጻ አልነበረም፥ (የአሁን (የዘመናችን) ቤተ ክርስቲያን መግለጫ፥ እነርሱ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ናቸው ነገር ግን ነጻ አይደሉም)። በአዳራሹ ፊት ለፊት አንድ መስበኪያ ሰገነት በአንድ በኩል እና በውስጡ አንድ ግዙፍ አረንጓዴ እባብ ያለው አንድ ትልቅ ጎጆ (ትልቅ የወፍ ጎጆ) በሌላኛው በኩል ያለው አንድ ግዙፍ መድረክ ነበረ፤ እና ተናጋሪው በሚቆምበት ቦታ ላይ ተንጠልጥሎ አንድ ታላቅ ሰይፍ በሁለት ሲባጎዎች ወደ ጎን ተንጠልጥሎ ነበረ፤ በመድረኩ ላይም የካህን ልብሶች ለብሰው 8 ወይም 10 የሚሆኑ በርከት ያሉ አገልጋዮች ነበሩ፥ አንዳቸው ከአንዳቸው ኋላ ተቀምጠዋል፥ አንዳቸው ከሌላኛቸው ትንሽ ብቻ ከፍ ብለው ተቀምጠዋል። የተሰበሰበው ሰው እነዚህን ሰዎች ተመልክቷል እና እነርሱም ቤተ ክርስቲያንን (የተሰበሰቡትን ሰዎች) ተመልክተዋል።



ከመስበኪያው ሰገነት አንድ ነጎድጓድማ ድምፅ እስኪሰማ ድረስ ለጥቂት ጊዜ ጸጥታ ነበረ፥ ከ**እግዚአብሔር** በቀጥታ እንደመጣ እንዲህ አለ:- ***“የእግዚአብሔርን ምክር በሙሉ ማን ያውጃል?”***

የመጀመሪያው ካህንም በእጁ አንድ መጽሐፍ ቅዱስ ይዞ ተነሣ፥ እርሱም እንዲህ ሲያደርግ፥ የቀደመው አረንጓዴ እባብ ከተጠቀለለበት ተፈታና በሚያብለጨልጩ ዐይኖቹና ባፈነገጡ የእባብ ጥርሶቹ በሰውየው ላይ የጥላቻ ድምፅ በማሰማት ተዘረጋ፤ በሐሰት **የእግዚአብሔር** ሰው ተብሎ የተጠራው ወደ ኋላ ወደ መቀመጫው አፈገፈገ እና መጽሐፍ ቅዱሱንም ከወንበሩ ስር አስቀመጠው። እባቡም አንገቱን ወደላይ ሲዘረጋና ሰይፉን ሲነካ ለዛ ሰው እንዲህ አለ:- ***“የእግዚአብሔርን ድምፅ የሚታዘዝ ማንኛውም ሰው፥ እኔ በዚህ ሰይፍ እገድለዋለሁ።”***

እና ለጥቂት ጊዜ፥ በድጋሜ ጸጥታ ነበረ። ከዛም ድምፁ በድጋሜ ከመስበኪያው ሰገነት ላይ ተሰማ፥ ***“የእግዚአብሔርን ምክር በሙሉ ማን ያውጃል?”*** ከዛም የካህን ልብስ ከለበሱት ሁለተኛው ሰው በመነሣት ወደ ፊት እንደመራመድ አለ፥ በድጋሜም እባቡ ወደ እሱ ተዘረጋበት፥ እሱም በፍርሀት ወደ ኋላ ወደቀና ተቀመጠ እና መጽሐፍ ቅዱሱን ከወንበሩ በታች አስቀመጠ (ቃሉን መደበቅ)። እባቡ በድጋሜ ሰይፉን ነካና በዚያው አስተያየት እንዲህ አለ:- ***“የእግዚአብሔርን ድምፅ ብትታዘዝ፥ እኔ እገድልሃለሁ።”***

እና ለሦስተኛ ጊዜ ድምፁ ከመስበኪያው ሰገነት አንጎደጎደ፥ እና ሦስተኛ ሰው ተነሣና ከሱ በፊት እንደነበሩት እንደ ሁለቱ ተቀመጠ። እያንዳንዱ ካህን እባቡን ለመቃወም አጋጣሚ እስኪያገኝ ድረስ በድጋሜ እና በድጋሜ ድምፁ አስተጋባ፥ ነገር ግን የመጀመሪያዎቹ ሦስቱ እንደተሸነፉት፥ ፍርሀት ሁሉንም አሸነፋቸው። እባቡም በክፉ (በመጥፎ) ፈገግታው ፈገግ አለ።

ከዛም ድምፁ በድጋሜ ከመስበኪያው ሰገነት እንዲህ እያለ ተሰማ:- ***"አህ አንድ ሰው ቢኖር ኖሮ፥ አህ አንድ ሰው ቢኖር ኖሮ፤ አህ የእግዚአብሔርን ምክር በሙሉ የሚያውጅ አንድ ሰው ቢኖር ኖሮ፥ እነዚህ የታሰሩ ሰዎች በተፈቱ ነበር! አንድ ሰው የለም እንዴ?"***

ከዛ አንድ ጥቂት ክብር ያለው (ዝቅ ያለ) ሰው (ማለትም እርሱ በዓለም እይታ ምንም ነበር)፥ ወደ መድረኩ ሄደና ከሰይፉ በታች ቆመ፥ እና እርሱ ዓይኖቹን ወደ ሰማይ አንሥቶ እንዲህ አለ:- ***"አ እግዚአብሔር አምላክ ሆይ፥ መንፈሴን በእጆችህ ውስጥ አደርጌአለሁ።"*** ከዛ እርሱ መጽሐፍ ቅዱስ ከፈተና አነበበ። እርሱ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንዳች ነገር አልጨመረም፥ አንዳች ነገርም ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አልቀነሰም፤ እርሱ **ቃሉን** (**የእግዚአብሔርን ቃል**) አነበበ፥ ሥልጣን እንዳለው ሰውም ተናገረ።



እርሱ እንደጨረሰም፥ የቀደመው እባብ ወደ ሰይፉ ጠርዝ ወደ ላይ ተዘረጋና ሰይፉን በቦታው ከያዙት ሲባጎዎች አንዱን ቆረጠ፥ ሰይፉም ወደ ታች ተወዛወዘና እርሱን ሳተው በራሱ ላይም አለፈ፤ ምክንያቱም እርሱ "በትሕትና ዝቅ ያለ፥ ጥቂት ክብር ያለው" ሰው ነበረ፤ የሰይፉም ክብደት ሌላኛውን ሲባጎ እንዲበጠስ አደረገው፥ ሰይፉም ወደ ኋላ ተወዛወዘና ተሰልፈው የነበሩትን የእነዚያን ካህናት ልብ ወጋና ግድግዳ ላይ ቸነከራቸው። ከመስበኪያው ሰገነትም የተስፋ መቁረጥ ታላቅ ጩኸት ተሰማ፤ ነገር ግን ከዛ የበለጠ የደስታ ጩኸት ከተሰበሰቡት ሰዎች ተሰማ፥ የእያንዳንዱ ሰው ሰንሰለት ተፈቶና እነርሱ ነጻ ወጥተው ነበር! (በ**ቃሉ** (**በእግዚአብሔር ቃል**) እነርሱ ነጻ ወጡ)።

ራእዩ ሲሰወር (ሲጠፋ)፥ አዳኙ በደመና ላይ ከራሴ በላይ ሆኖ ሌላ ራእይ አየሁ። እርሱ እንዲህ በማለት ተናገረ:- "***ልጄ ሆይ የእነዚህን ነገሮች ትርጉም (ፍቾች) ስማ። ያየኸው የስብሰባ አዳራሽ የአምልኮ መልክ ያለው ኃይሉን ግን የካደ ዓለማዊ (ሥጋዊ) ቤተ ክርስቲያን ነው። እነርሱ በዚህ ዓለም የደስታ ጌጣ ጌጦች በሙሉ ተሸፍነዋል፥ ለብራቸውና ለወርቃቸውም መጨረሻ የለውም። ያየኻቸው ሰዎች፥ እኔ ለእነርሱ የምትሁላቸው ናቸው፥ ነገር ግን ሕዝቤ እውቀት ከማጣቱ የተነሣ ጠፍቶአል፤ እነርሱ ዐይን አላቸው፥ ግን አያዩም፤ እነርሱ ጆሮ አላቸው፥ ግን መስማት አይችሉም። እነርሱ የእውነት በእስራት ውስጥ ናቸው እና ነጻ መውጣት አለባቸው! ካህናቱ ተቀምጠውበት ያየኸው መድረክ፤ መድረኩ መነሻቸውን ከጥልቁ የሲኦል ጉድጓድ ያገኙ፥ እውነታውን ሳያገኙ አስቀድመው የሆኑ አሳቦች ነው። መስበኪያው ሰገነት የእግዚአብሔር ዙፋን ነው፤ እባቡም፥ ራሱ የቀደመው ሰይጣን ነው። ያየኸው ሰይፍ የእግዚአብሔር ቃል ነው፤ ተንጠልጥሎበት የነበረው ሲባጎዎችም ትርጉም ሕይወትን ለመስጠት ቃሉ ያለው ኃይል ወይም ሕይወትን ለመውሰድ ቃሉ ያለው ኃይል። ለባለ ጥቂት ክብር ሰውዬ ሕይወት ተሰጥቶት ነበረ እና ቃሌን ከማይሰብኩ ካህናት ሕይወት ተወሰደ! ያየኻቸው ካህናት፥ ከእያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን እኔን ያወቁ (የሚያውቁ) የሚያስመስሉ ወንዶች (እና ሴቶች) ናቸው፥ እነርሱ ግን በሕይወት መጽሐፍ ላይ ያልተፃፉ ነገሮችን ለሕዝቤ ያስተምራሉ፤ ትዕቢታቸውና መዳፈራቸው፣ እና ዓለማዊ መንፈሳቸው፥ ውሸተኛና የውሸቶች አባት የሆነውን ሰይጣንን እንዲታዘዙት ያስገድዳቸዋል፤ እያንዳንዳቸውም ካህናት ሞከሩና ሌሎቹን በማሸብረቅ፣ በረጅም ጽሑፎች፣ በክርክር እና በመሳሰሉት በለጡ፤ ነገር ግን እነሱ የተመለከቱት የቃሉን "ጽሑፍ" ብቻ ነው፥ እና የቃሉን "ሕይወት" ተዉት። ልክ እንደዚህ ሁሉም የሚጠፉበት ቀን ይመጣል፥ አሁንም ቀርቧል።***"

ይህን አስከፊ (አሰቃቂ) ሁኔታ ከተመለከትሁ በኋላ፥ **ጌታ** በድጋሚ በእነዚህ ቃላት ተናገረ፥ ***በትንቢተ [ኤርምያስ 23](#) ውስጥ ያሉትን ቃሎቹን፥ እንዲሁም በትንቢተ [ሕዝቅኤል 34](#) ውስጥ ያሉትን ቃሎቹን ታስታውሳለህ?*** **ኢየሱስ**:- አንብበው አለ።

እኔም መጽሐፍ ቅዱሴን ከፈትሁና አነበብሁ፥ "*የማሰማርያዬን በጎች ለሚያጠፉና ለሚበትኑ እረኞች ወዮላቸው! ይላል እግዚአብሔር።*" ([ኤርምያስ 23:1](#))። በነቢያት አስከፊ (አሰቃቂ) ነገር አይቻለሁ፥ እነሱ ዝሙት ይፈፅማሉ በውሸትም ይሄዳሉ: (**የእግዚአብሔርን ቃል** ማዛባት)፥ እና የክፉ አድራጊዎችን እጆች ያጸናሉም (ያበረታሉም)። ([ኤርምያስ 23:14](#))። **ኢየሱስ** እንዲህ አለ:- "***በቀናት ፍጻሜ ላይ ይህን ትረዳለህ። ራሳቸውን ለሚመግቡ (ለሚያሰማሩ) እረኞች ወዮላቸው፥ እረኞች መንጋውን መመገብ (ማሰማራት) አይገባቸውም እንዴ!***" ([ሕዝቅኤል 34:2](#))። *የደከመውን አላጸናችሁትም የታመመውንም አላከማችሁትም የተሰበረውንም አልጠገናችሁትም የባዘነውንም አልመለሳችሁትም የጠፋውንም አልፈለጋችሁትም በኃይልና በጭቆናም ገዛችኋቸው።* ([ሕዝቅኤል 34:4](#))። *የወፈረውንና የበረታውንም አጠፋለሁ፤ በፍርድም እጠብቃቸዋለሁ።* ([ሕዝቅኤል 34:16](#))። ከዛ እርሱ ለኔ እንዲህ አለ:- ***እነዚህ የውሸት እረኞች ሰይፉ እላያቸው ላይ ሲወድቅ በምንም መልኩ አያመልጡም። በጎቼ ግን ማስጠንቀቂያው የግድ ሊነገራቸው ይገባል፥ እነርሱ (በጎቼ) ነጻ መውጣት አለባቸው!*** በድጋሜም እርሱ እንዲህ አለ:- ***በትንቢተ ኤርምያስ ምዕራፍ 25 መጨረሻ ክፍል ውስጥ ያለውን የእኔን ቃል ታስታውሳለህ? አንብበው!***

እኔም እነዚህን ቃላት አነበብሁ፥ *በዚያም ቀን የእግዚአብሔር ግዳዮች ከምድር ዳር ጀምሮ እስከ ምድር ዳር ድረስ ይሆናሉ፤* ([ኤርምያስ 25:33](#))። *እናንተ እረኞች አልቅሱ፥ ትታረዱ ዘንድ ቀኑ መጥቷል!* ከዛ እርሱ እንዲህ አለኝ:- ***እነዚህ ቀናት በፍጥነት ይመጣሉ፥ እረኞች ያለቅሳሉ፥ አዎ፥ በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል፤ ሰይፉ ሲወድቅ ግን ለዘላለም በጣም የረፈደ ይሆናል። ጥቂት ክብር (ዝቅ ብሎ፥ little stature) ኖሮት ያየኸው ሰው፥ ራሱን ወይም ራሷን በትሕትና ዝቅ የሚያደርግ (የምታደርግ)፥ እና መታመኑን (መታመኗን) በእግዚአብሔር በማድረግ እስከ መስቀል ሞት ድረስ እንኳ ታዛዥ የሚሆን (የምትሆን)፥ እና የእግዚአብሔርን ሙሉ ምክር በሙሉ ኢያወጀ (ኢያወጀች) ወደ ፊት የሚሄድ (የምትሄድ) ማንኛውም ሰው ነው (ናት)! አ፥ እንደዚህ አይነት ሰው ማግኘት ብችል፤ እንደዚህ አይነት አንድ ሰው የት እንዳለ ልትነግረኝ ትችላለህ? በእንዲህ አይነት ሰው ሰማይና ምድርን ማንቀጥቀጥ እችላለሁ፥*** ይላል **ጌታ**።

ፍጻሜ።

**ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ የነበረውና ያለው የሚመጣውም ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ። የታረደው በግ ኃይልና ባለ ጠግነት ጥበብም ብርታትም ክብርም ምስጋናም በረከትም ሊቀበል ይገባዋል፤ በረከትና ክብር ምስጋናም ኃይልም ከዘላለም እስከ ዘላለም በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው፥ ለበጉም ይሁን። በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው ለአምላካችንና ለበጉ ማዳን ነው። አሜን፥ በረከትና ክብር ጥበብም ምስጋናም ውዳሴም ኃይልም ብርታትም ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ለአምላካችን ይሁን፤ አሜን። ሃሌ ሉያ። የዮሐንስ ራእይ 4:8፤ 5:12 (14)፤ 7:10 (12)። ቅድስና ለእግዚአብሔር፥ አሜን፥ ሃሌ ሉያ።**

**አንድ አምላክ ለሆነ ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ክብር ምስጋና ውዳሴ አምልኮ ኃይል ይሁን፤ ሃሌ ሉያ፥ አሜን**

**የእስራኤል አምላክ የሠራዊት ጌታ፥ የእግዚአብሔር አብ ቃል፥ የነገሥታት ንጉሥና የጌቶች ጌታ ቅዱስ እግዚአብሔር የናዝሬቱ** ኢየሱስ ክርስቶስ የልጁን የቶማስ ቶሙከዳህታን አካል ተጠቅሞ ተረጎመው። hithomasgetachew@gmail.com